# የትምህርት ቤት ክልል የፍጥነት መቆጠሪያ ካሜራ ፕሮግራም ከመስከረም 18 ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል

የአሌክሳንደሪያ ከተማ አዲሱ የትምህርት ቤት ክልል የፍጥነት መቆጠሪያ ካሜራ ፕሮግራም ተግባራዊ የሚደረግ ከመሆኑም በተጨማሪ ከሰኞ፣ መስከረም 18 ጀምሮ መጥሪያ መስጠት ይጀምራል። የፍጥነት መቆጠሪያ ካሜራዎቹ በሚከተሉት የትምህርት ቤት ክልሎች ውስጥ ይተከላሉ፡-

- **ፍራንሲስ ሀሞንድ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Francis Hammond Middle School)** (ሴሚናሪ መንገድ/Seminary Road በኬንሞር መንገድ/Kenmore Avenue እና በኖርዝ ጆርዳን መንገድ/North Jordan Street መካከል)
- **ጆን አዳምስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (John Adams Elementary School እና ፈርዲናንድ ቲ. ዴይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/ Ferdinand T. Day Elementary School)** (ኖርዝ ቢውሪጋርድ መንገድ/North Beauregard Street በኖርዝ ሀይ ቪው ሌን/North Highview Lane እና ሪዲንግ መንገድ/ Reading Avenue መካከል)
- **ጆርጅ ዋሽንግተን መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (George Washington Middle School)** (ማውንት ቬሮን መንገድ/Mount Vernon Avenue በፍራዶክ መንገድ/Braddock Road እና ሉሬይ መንገድ/ Luray Avenue መካከል)




አንዳንድ ተጨማሪ ማወቅ የሚገቡ ዋና ዋና መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡

- የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎቹ የሚሰሩት የፍጥነት ገደብ ምልክት መስጫ መብራቶች ሲበሩ ብቻ ነው።
- የእያንዳንዱ የትምህርት ቤት ክልል ርዝመት ወደ ¼ ማይል ሲሆን 15 MPH የፍጥነት ገደብ አለው።
- መጥሪያዎች $100 ዋጋ የሚያስከፍሉ ሲሆን በመልእክት ይላካሉ።

- ምልክቶች ለአሽከርካሪዎች የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራ ክልል ውስጥ መግባታቸውን ለማሳወቅ ይተከላሉ።
- መጥሪያ በመልእክት ከደረስዎት ክፍያዎን ለመክፈል ወይም ተቃውሞዎን ለመግለጽ በመጥሪያው ላይ ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ።

ከተማው በሰኔ ወር የ2022-2023 ዓ.ም የትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ የሁለት ሳምንታት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ሙከራ ያካሄደ ሲሆን ተጨማሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ሙከራ ከነሐሴ 21 እስከ መስከረም 15 ያካሂዳል።

ከተማው የግጭት ታሪክን፣ የትራፊክ ፍሰትን፣ የተሽከርካሪዎች ፍጥነትን፣ እና የተማሪዎች እድሜና ብዛትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ዳታ ተኮር አሰራርን በመጠቀም የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራ የሚተከልባቸውን ቦታዎች መርጧል።

የአሌክሳንደሪያ ከተማ ካውንስል በጥቅምት 2022 በትምህርት ቤት ክልሎች ውስጥ እና በስራ ክልሎች ውስጥ የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎችን መጠቀምን የሚፈቅድ ደንብ ያጸደቀ ከመሆኑም በተጨማሪ ለአምስት የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎች የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ በ2023 ዓ.ም በጀት ዓመት የጸደቀው በጀት ውስጥ ተካቷል።

ከተማው ደህንነታቸው የተጠበቀ የትምህርት ቤት መንገዶች (Safe Routes to School) ለማቅረብ ቁርጠኛ ሲሆን የተሽከርካሪ ፍጥነት በወላጆች እና አሳዳጊዎች ስለ ልጆቻቸው ወደ ትምህርት ቤት በእግር ወይም በብስክሌት መሄድ በተመለከተ ሲጠየቁ ከተጠቀሱት ዋና ዋና ችግሮች መካከል አንዱ ነው። እንደ የዩኤስ የትራንስፖርት መምሪያ (USDOT) የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎች Sየግጭቶችን መጠን በ50% እንደሚቀንሱ የተረጋገጠላቸው አስተማማኝ መቆጣጠሪያ ናቸው። በተጨማሪም የተፋጠነ ተፈጻሚነቱ ከተማውንበሌሎች ከፍተኛ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ቦታዎች የፖሊስ ሀብቶችን እንዲጠቀም ያስችለዋል።

የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራዎች የራዳር ቴክኖሎጂን በመጠቀም የፍጥነት ገደብ ጥሰቶችን በፍጥነት ይመዘግባሉ። ቃለ መሃላ የገባ የህግ አስከባሪ መኮንን ጥሰቱን ካረጋገጠ በኋላ የፍጥነት መተላለፍ ቅጣት ለተሽከርካሪው ባለቤት፣ ተከራይ ወይም ተከራይ በፖስታ ይላካል።

ስለ ከተማው የፍጥነት መቆጣጠሪያ ካሜራ ፕሮግራም የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት alexandriava.gov/go/3785 ይጎብኙ።